# <u>የኢትዮጵያ አገራዊ ንቅናቄ ምስረታ ኮንፈረንስ ተብየው በሽግግር ምስረታ ሽፋን በኢትዮጵያ ሕልውናና በሕዝቧ ፀረ ወያኔ አመፅ ላይ ከፍተኛ ትሪዝን ፈጽሟል።</u>

ከአስተዋይ በቀለ

ከፉንና ደጉን መለየት አገርን ያድናልና ሁልህም ልብ በል !

በሽግግር ሥርዓት ምስረታ ሽፋን የተንቀሳቀሰው የኢትዮጵያ አገራዊ ንቅናቄ ምስረታ ተብየው ፣ የብፁዓን አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ከቅንነት የመነጨ አርቆ አሳቢነት ሳይሆን፤ በባዕዳን መሰሪ ስትራተጂክ ትኩረትና በሻቢያ አፍራሽ አጀንዳ ተፀንሶ ዘጠኝ ወር ሙሉ በረቂቅ ሴራ ተገምዶና ተክኖ የተፈጠረ ፀረ-ኢትዮጵያ ነው።

ሥራውን የጀመረው ግልብጥ ወያኔ የሆኑትን ግንቦት 7ንና ቀንደኛ ኦነጐችን ፣ቅጥረኞችንና ዘላባጅ ቀባጣሪ ግለሰቦችን በማስተባበርና በማፈራረም ሲሆን፣ ካለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ፈቃድና ማንዴት ለኦነግ የመገንጠል አጀንዳ፣ ባንዲራና ቋንቋ ይፋ እውቅና በመስጠት ቀንደኛ ኦነጐች አላማቸውን እንዲያሳኩ የኢዮጵያን አገራዊ ሽግግር ምስረታን ወሳኝ አመራር በበላይነት እዲይዙት አድርጓል።

ወቅታዊ ዓላማውና ትኩረቱ አገር ውስጥ ያለውን ሕዝባዊ አመፅ ቀምቶ በግንቦት 7ና በአጋሮቹ ኦነጐች አመራር ስር እንዲውል ማድረግ ሲሆን ፤መድረሻ ግቡ ደግሞ ወያኔን አውርዶ ብርሃኑን ርእሰ ብሔር በማድረግ ቀደም ሲል በግንቦት 7ና በአጋሮቹ ኦነጐች መካከል በተደረገው የምስጢር ሜሞራንደም መሰረት የኦሮሞን ክልል ወደ ሉዓላዊ አገርነት ከፍ አድርጐ እውን ማድረግና ቀሪዋን ኢትዮጵያን ደግሞ ለሻቢያ ኤርትራ የማታሰጋ አገር አድርጐ መከፋፈልና ለሌሎች ብሔረሰቦች ማቀራመት እንደሆነ የዉስጥ ጥቆማ አረጋግጧል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን ሴራ ለማዳፈን በያለበት ሁሉ ዘብ ቆሟል። እግዚአብሔር መተማመኛው ስለሆነ በኢትዮጵያ አገራዊ ንቅናቄ ምስረታና አፈራርሞ ባሰለፈበት ጠላቶቹ ላይ ድል እንደሚነሳ ጥርጥር የለውም።

## ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነትና አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ ሰንደቅዓላማ

## ዘላለማዊ ነው ! ! !